የ OMB መቆጣጠሪያ ቁጥር 1920-1303
የቅፁ ማብቂያ: 09/30/2021

# የመልቀቂያ ጥበቃ መግለጫ

የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከያ ማዕከላት (Centers for Disease Control, CDC) እርስዎ ከሚኖሩበት ቦታ እንዳይባረሩ ወይም እንዳይወገዱ ሊከላከልልዎት የሚችል ትእዛዝ አስተላልፈዋል። **ይህ ማለት ብቁ ከሆኑ እስከ ጁላይ 31, 2021 ድረስበሚኖሩበት ቦታ መቆየትይችሉ ይሆናል።**

## ይህንን ቅጽ እንዴት እንደሚጠቀሙ

1. በ CDC ትዕዛዝ መሠረት ከቤት የማስወጣት ጥበቃን ብቁ መሆንዎን ይመልከቱ።
   ከባለሙያ እርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ በ (800) 569-4287 ይሂዱ ወይም በአከባቢው HUD ፍቃድ ያለው የቤቶች አማካሪ የእውቂያ መረጃ ለማግኘት https://www.hudexchange.info/programs/housing-counseling/rental-eviction/ ይዳሱ።
2. ብቁ መሆንዎን የሚገልጽ መግለጫን በቀጣዩ ገጽ ላይ ይፈርሙ።
3. የተፈረመበትን የመግለጫ ገጽ ለተከራዩበት ግለሰብ ወይም ኩባንያ (ለምሳሌ፣ የህንፃ አስተዳደር፣ አከራይ፣ ወዘተ) ይስጡ። የመዝገቦችን ፎቶ ወይም ቅጅ ይያዙ እናም ችግር ካለ ወደ ባለሙያዎ መልሰው ይደውሉ።

---

## 1. ብቁ ነኝ?

*በእያንዳንዱ አምድ ውስጥ ቢያንስ አንድ ሳጥን ላይ ምልክት ማድረግ ከቻሉ ብቁ ይሆናሉ።*

### *አምድ ሀ*

- ☐ በ 2020 ወይም በ 2021 የማነቃቂያ ቼክ (የኢኮኖሚ ተፅእኖ ክፍያ) ተቀብያለው
- ☐ በ 2020 ለ IRSምንም ዓይነት ገቢ ሪፖርት ማድረግ አልተጠበቀብኝም ነበር
- ☐ በ 2020 ወይም በ 2021፣ እንደግለሰብ ከ $99,000 ዶላር **በታች** ወይም በጋራ ከ $198,000 ዶላር **በታች** ነው ያገኘሁት (ወይም አገኛለሁ ብዬ እጠብቃለሁ)

  ከሚከተሉት ጥቅማጥቅሞች የሚያገኙ ከሆነ በዚህ መጠን በታች ያገኙ ይሆናል፥
  - የተጨማሪ ምግብ ድጋፍ መርሃግብር (SNAP)
  - ለተቸገሩ ቤተሰቦች ጊዜያዊ ድጋፍ (TANF)
  - የተጨማሪ ደህንነት ገቢ (SSI)
  - የማህበራዊ ደህንነት አካል ጉዳት ኢንሹራንስ (SSDI)

**ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዳቸውም አይደሉም — ብቁ አይደሉም**

*እና*

### *አምድ ለ*

ሙሉ ኪራይ መክፈል ወይም ሙሉ የቤት ክፍያ መክፈል አልችልም ምክንያቱም፥

- ☐ የቤቴ ገቢ በከፍተኛ ደረጃ ወርዷል
- ☐ ከሥራ እንድባረር ተደርጊያለው
- ☐ የሥራ ሰዓቴ ወይም ደሞዜ ተቆርጧል
- ☐ ከአቅሜ በላይ ከፍተኛ የሆነ የሕክምና ወጪዎች አሉኝ[1]

**ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዳቸውም አይደሉም — ብቁ አይደሉም**

**በእያንዳንዱ አምድ ውስጥ ቢያንስ አንድ ንጥል ላይ ምልክት አድርገዋል?**
**የእርስዎ የገቢ ደረጃ ብቁ ነው።**

[በሚቀጥለው ገጽ የመጀመሪያው ሣጥን ላይ ምልክት ያድርጉ]

---

[1]ለዓመቱ ከተስተካከለ አጠቃላይ ገቢዬ 7.5% ወይም ከዚያ በላይ የሚባል

## 2. ብቁ የመሆኔ መግለጫ

ከዚህ በታች ያሉትን ሳጥኖች ላይ ምልክት በማድረግ እያንዳንዱ መግለጫ እውነት መሆኑን አውጃለው።

- ☐ የገቢ ደረጃዬ ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች ብቁ ነው።
- ☐ ከሙሉ ክፍያ ጋር በተቻለ መጠን በጣም የተቀራረበ ወቅታዊ ከፊል ክፍያዎችን ለመፈፀም እና የቤት ኪራይ ወይም የመኖሪያ ቤት ክፍያን ለመፈፀም የመንግስት ድጋፍን ለማግኘት የተቻለኝን ሁሉ አድርጌያለሁ።[2]
- ☐ ከተባረርኩ ሌላ የመኖሪያ ቤት አማራጮች የሉኝም፣ ስለዚህ፥
  - ምናልባት ቤት-አልባ ልሆን እችላለው፣, **<u>ወይም</u>**
  - ወደ ቤት-አልባ መጠለያ መሄድ ይኖርብኛል፣, **<u>ወይም</u>**
  - በአቅራቢያ ካሉ ሰዎች ጋር አብሬ መኖር ይኖርብኛል።.
- ☐ ከፈረምኩ በኋላ የሚከተሉትን እረዳለው፥
  - ከአከራዬ ጋር ስምምነት እስካላደረኩ ድረስ፣ እኔ አሁንም የኪራይ፣ የኋላ ኪራይ እና በኪራይ ውል ውስጥ ለሚገኙ ማናቸውም ክፍያዎች፣ ቅጣቶች ወይም ወለዶች ተጠያቂ ነኝ።
  - የኪራይ ውሎቼን አሁንም መከተል ይኖርብኛል።
  - ከአከራዬ ጋር ስምምነት እስካላደረኩ ድረስ፣ የሚያስፈልገኝን ክፍያ መፈጸም ካልቻልኩ፣ ይህ ለግዜው የተቋረጠ የማፈናቀል ሥራ ሲያልቅ ከቤት ውስጥ ልወጣ እችላለው።
  - የቤት ኪራይ ያለመክፈል ወይም የመኖሪያ ቤት ክፍያ ያለመክፈል ውጪ ለሆኑ ምክንያቶች ልባረር እችላለው።

### ለተከራዮች መላ መፈለጊያ መሳሪያዎች

**ድንገተኛ የኪራይ ገንዘብ ድጋፍ ያግኙ**
በአካባቢያዊ HUD ፍቃድ ላገኙ የቤት አማካሪዎች ዝርዝር ለማግኘት (800) 569-4287 ላይ ይደውሉ

**በእዳ አሰባሰብ ላይ ችግሮችን ሪፖርት ያድርጉለ**
CFPB cfpb.gov/complaint ቅሬታ ያቅርቡ

**አድልዎ ሪፖርት ያድርጉ**
ቅሬታ ያስገቡ። ለ HUD በ (800) 669-9777 ይደውሉ

***ይህንን መግለጫ የምፈርመው የሐሰት ምስክርነት ቅጣት ስር ነው። ያ ማለት ከላይ ያሉት መግለጫዎች እውነት መሆናቸውን ቃል እገባለሁ እናም በመዋሸት በወንጀል ልቀጣ እንደምችል እረዳለው።***

እዚህ ይፈርሙ፥:

X ______________________________ ቀን: ______________

## 3. ይህንን የተፈረመበት ገጽን ለተከራዩት ግለሰብ ወይም ኩባንያ ይስጡ።

*__ATTN የቤት አከራዮች፥__ ስለ ተገዢነትዎ እናመሰግናለን። የ CDC'ን የማስለቀቂያ መከላከያ ትእዛዝ ከጣሱ, እርስዎ እና/ወይም ንግድዎ የገንዘብ ቅጣት እና የእስራት ጊዜን ጨምሮ የወንጀል ቅጣት ሊጣልብዎት ይችላሉ።*

---

[2]ለአካባቢዎ ባለሙያ መደወል ለእርስዎ የሚገኘውን ሁሉንም እርዳታ ለማወቅ ከሁሉ የተሻለው መንገድ ነው። (800) 569-4287 ላይ በመደወል በአከባቢው HUD ፍቃድ ያገኘ የቤቶች አማካሪ ዝርዝርን ያግኙ።

[3]ከቤት የማስወጣት እገዳ ማቋረጫ መግለጫን ቀደም ብለው ፈርመው ከሆነ፣ ሌላ ማስገባት አያስፈልግዎትም።.